አነስተኛ ድርሻ ላላቸው ባለአክሲዮኖች የሚደረግ ጥበቃ

የአሰልጣኞች ስልጠና

በላይሁን ይርጋ

ከፍተኛ የፖሊሲ እና ሕግ አማካሪ

belayhunyirga2@gmail.com

0912418717

አነስተኛ ድርሻ ላላቸው ባለአክሲዮኖች ጥበቃ ለምን አስፈለገ?

- የካፒታል ዕጥረት እና የተገኘውን ያክል ሃብት አሟጦ በተቀናጀ እና በተደራጀ መልክ በስራ ላይ የማዋል አስፈላጊነት
- በንግድ አመችነት ረገድ በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪ የመሆን አስፈላጊነት

- በኩባንያዎች ውስጥ አነስተኛ ድርሻ ባላቸው ባለአክሲዮኖች ላይ የሚደርሱ ዓይነተኛ ችግሮች፡-

    1) ምዝበራ/ዘረፋ

    2) መረጃ የማጣት/ ግልጽነት አለመኖር

    3) በውሳኔ አሰጣጥ ረገድ ዓቅመቢስ መሆን

    4) አጥፊ አመራሮችን ተጠያቂ ለማድረግ ያለመቻል

    5) የአክሲዮኖቻቸው ዋጋ ከተገቢው የማነስ እና ከማህበሩ በመውጣት ረገድ የሚገጥማቸው የተለየ ችግር

አነስተኛ ድርሻ ያላቸውን ባለአክሲዮኖች ከጉዳት ለመጠበቅ ሕጉ መነሻ ያደረጋቸው መርሆዎች

- ለጥቅም ግጭት መንስዔ ሊሆኑ ስለሚችሉ ግንኙነቶች እና ውሎች የተሟላ መረጃ የሚገኝበት ስርዓት ማበጀት
- የኩባንያ ዳይሬክተሮች እና አመራሮች ግዴታዎችን በግልጽ ማስቀመጥ
- አነስተኛ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች በቀላሉ ምርመራ ለማድረግም ሆነ ክስ ለመመስረት የሚችሉበት ስርዓት መዘርጋት

- በውሳኔ አሰጣጥ የአናሳ ባለአክሲዮኖች ተሳትፎን ማጎልበት
- አናሳ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች ከማጎበሩ የሚወጡበት ዕድል ማስፋት
- ከነዚህ ውስጥ የተወሰኑት ለምሳሌ የዳይሬክተሮች ግዴታዎች፣ በዳይሬክተሮች ላይ ክስ ስለሚቀርብበት ሥርዓት ወዘተ የማጎበሩን አስተዳደር በተሞለከተ በተደረገው ውይይት ተሸፍኗል።

ከውል አፈጻጸም ጋር በተያያዘ የሚሰጥ ጥበቃ

- ከማኅበሩ ጋር ቅርበት ካላቸው ሰዎች(306/6/፣311፣312 እና 313) የሚደረግ ውል ከማኅበሩ ሃብት አስር በመቶ በታች የሚወክል ሲሆን ስለሚደረግ ጥበቃ (306/1 እስከ 5፣323)፣ v. 356)
- የጥቅም ግጭት ሊያስነሳ የሚችል ውል ከማኅበሩ ሃብት አስር በመቶ እና ከዛ በላይ የሚወክል ሲሆን ስለሚደረግ ጥበቃ (395)
- የጥቅም ግጭት ባይኖርም የሚደረገው ውል በአንድ ጊዜ ወየም በተለያዩ ግዜዎች በአንድ ዓመት ውስጥ ከማኅበሩ ሃብት 51 በመቶ እና ከዛ በላይ የሆነን መጠን ማስተላለፍ የሚያስከትል ሲሆን ስለሚደረግ ጥበቃ (394(4))

ልዩ ምርመራ እንዲደረግ የመጠየቅ መብት

- የማኅበሩ ዋና ገንዘብ 10 በመቶ የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ጥያቄ ያቀረቡ እንደሆነ የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የማኅበሩ የስራ አመራር አነስተኛ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖችን ወይም ማኅበሩን በሚጎዳ አኳሃን መመራት አለመመራቱን የሚያረጋግጥ ኢንስፔክተር መመደብ ያለበት ስለመሆኑ (355(1)
- የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በራሱ ተነሳሽነት የተወሰኑ ባለአክሲዮኖች መብት የሚጎዳ ድርጊት መፈጸም አለመፈጸሙን ለማረጋገፅ ኢንስፔክተሮችን መሾም ስለመቻሉ (357)

ልዩ ምርመራ እንዲደረግ የመጠየቅ መብት … የቀጠለ

- በተጨማሪም ማንኛውም ባለአክሲዮን “ተለይተው የተመለከቱ የማኅበሩ ስራዎች በማኅበሩ እና ባለአክሲዮኖች ላይ ያላቸውን ተጽዕኖ እንዲሁም ከሕግ እና መልካም የንግድ አሰራር አንጻር ምን ያህል ተገቢ እንደሆኑ መርምሮ ሪፖርት የሚያቀርብ ልዩ መርማሪ እንዲሾም ለማኅበሩ መደበኛ ጉባዔ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል።” (396/1)
- የማኅበሩ ጉባዔ ልዩ መርማሪ ካልሾመ የማህበሩን ካፒታል 10 በመቶ የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ጥያቄውን ለፍ/ቤት ማቅረብ ይችላሉ። ፍ/ቤቱ ልዩ መርማሪ መሾም ያለበት ሲሆን የምርመራውን አድማስ ግን በማኅበሩ ጥቅም ላይ ከባድ ጉዳት የሚደርስ ከሆነ መገደብ ይችላል። (396/3/)

ከባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ጋር በተያያዘ የተሰጡ ጥበቃዎች

- ልዩ ጥቅም ስለሚያስገኙ አክሲዮኖች የተደነገገው (278፣279 v. 335፣ 336) እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላላ ጉባዔ ለተወሰኑ ማኅበርተኞች ያልተገባ ጥቅም የማስገኘት ውጤት ሊኖረው እንደሚችል ግልጽ የሆነ ውሳኔ ማስተላለፍ የማይችል ስለመሆኑ (364)
- የማኅበሩ ዋና ገንዘብ 10 በመቶ የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ጥያቄ ያቀረቡ እንደሆነ የማኅበሩ ኦዲተር ስብሰባ የመጥራት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ (351(2) v. 377(2))
- በተመሳሳይ የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የማኅበሩ ዋና ገንዘብ 10 በመቶ በሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ጥያቄ ሲቀርብለት ጠቅላላ ጉባዔ የመጥራት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ (366/2/)

ከባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ጋር በተያያዘ የተሰጡ ጥበቃዎች ... የቀጠለ

- የማኅበሩን ዋና ገንዘብ 5 በመቶ የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች ጥያቄ ያቀረቡለት እንደሆነ ጥያቄው ተገቢ መስሎ ከታየው ፍ/ቤት ጠቅላላ ጉባዔ እንዲደረግ ጥሪ የሚያደርግ እና አጀንዳ የሚያዘጋጅ ሰው መመደብ የሚችል መሆኑ (366/3/)
- ከማኅበሩ ዋና ገንዘብ 5 በመቶ የሚወክሉ ባለአክሲዮኖች የጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳ ማስያዝ የሚችሉ ስለመሆናቸው (372/2/)

- በማንኛውም ጊዜ ባለአክሲዮኖች ሊያገኙዋቸው ስለሚገቡ ሰነዶች በአንቀጽ 381 ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በጉባዔ ላይ እንደ አጀንዳ በቀረበ ጉዳይ ላይ ከድምዳሜ ለመድረስ የሚያስፈልግ ተጨማሪ መረጃ እንዲቀርብለት ማንኛውም ባለአክሲዮን ጥያቄ ማቅረብ ካስፈለገም ክስ መመስረት ይችላል (382/1/ እና /2/)
- መረጃው ይፋ መደረጉ በሕግ የተከለከለ ከሆነ ወይም ማኅበሩ ላይ ቀላል የማይባል ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ መረጃው ይፋ አይደረግም። ይህን የማስረዳት ሸክም የተጠለው በማኅበሩ አመራር ላይ ነው። (382/1 እና /2/)

ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የባለአክሲዮኖችን ተሳትፎ ማረጋገጥ

- አነስተኛ ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች ካላቸው ውሱን መረጃ፣ ተጽዕኖ እና ተጠቃሚነት አንጻር በማጎበሩ ስብሰባዎችም ሆነ ሌሎች መድረኮች በንቃት ለመሳተፍ አይበረታቱም።
- ሕጉ መረጃን፣ የስብሰባ ጥሪን፣ የስብሰባ ክንውን እና መሰል ሂደቶችን በኤሌክትሮኒክ ዘይቤ ማድረግ በማስቻል ተሳትፎዋቸውን ያበረታታል።
- የስብሰባ ጥሪዎች ባለአክሲዮኑ ለዚሁ ዓላማ በሰጠው ኢሜይል ወይም ሌላ አስተማማኝ የኤሌክትሮኒክ ዘዴ ወይም በሌላ የበለጠ አመቺ በሆነ መንገድ እንዲደርሰው ይፈቅዳል 367(2)(4)፤

ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የባለአክሲዮኖቸን ተሳትፎ ማረጋገጥ ... የቀጠለ

- በባለአክሲዮኖች ጉባዔ ላይ በአካል፣ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ወይም ሁሉም ባለአክሲዮኖች ከተስማሙ ስብሰባ ማድረግ ሳያስፈልግ ለውሳኔ በቀረበ ጉዳይ ላይ ሀሳባቸውን በጽሁፍ ወይም በኤለክትሮኒክ ዘዴ መስጠትን ይፈቅዳል (362/2/)
- በተለይ ድረ-ገጽ የተመለከቱ ድንጋጌዎች (493 እና 494)

- እያንዳንዱ የአክሲዮን ማኅበር ድረ-ገጽ እንዲኖረው እና በድረ-ገጹ ይፋ መደረግ ያለባቸውን መረጃዎች ይዘረዝራል፤
- በተጨማሪም ለባለአክሲዮኖች አስፈላጊ የሆኑ የማኅበሩን ጥቅም ላልተገባ ጉዳት የማይዳርጉ ሌሎች መረጃዎች እንድይዝ ያስገድዳል፤
- የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ጥሪዎች በድረ-ገጹ በኩል በተጨማሪነት እንዲጠሩ ይደነግጋል፤ በተቻለ መጠን በኤለክትሮኒክ መንገድ ጉባዔ እንዲደረግ እና ድምጽ መስጠት እንዲቻል የሚያስችል እንዲሆን ያስገድዳል።

ከማኅበሩ የመውጫ ዕድሎች

- የማኅበሩ ዋና ገንዘብ ዘጠና በመቶ በአንድ ባለአክሲዮን የተያዘ እንደሆነ ማኅበርተኛው አክሲዮኖችን እንዲገዛቸው በአናሳ ባለአክሲዮኖች የሚቀርበው ጥያቄ እና አተገባበሩ (296)
- የማሕበሩን ዋና ገንዘብ ዘጠና በመቶ የሚወክሉ አክሲዮኖች በቀጥታ በአንድ ባለአክሲዮን ባይያዙም በተዘዋዋሪ መንገድ በእናት ኩባንያ ከተያዘ በተቀጥላው ውስጥ ያሉ አናሳ ባለአክሲዮኖች አክሲዮናቸው እንዲገዛላቸው በፍ/ቤት ማስገደድ ይችላሉ (562)
- ከማኅበሩ አክሲዮኖች 50 በመቶ የሚገዛ ሰው ሲገኝ አክሲዮኖችን ተጫርቶ የመሸጥ መብት (293)
- ተጓዳኝ የሆነው አክሲዮኖችን ገዝቶ አናሳ ባለአክሲዮኖችን የማስወጣት መብት (294 እና 558)

አመሰግናለሁ!!!